# አዳም እና ሔዋን

## ዘፍ. ፩፥፳፮ - ፫፥፳፬

### አዳም

አምላኬ በደልኩህ ጥፋት ጀማመረኝ፣
የአንተን ቃል ዘንግቼ የሰው ቃል አሠረኝ።
ለኔ ያደረግኸው መልካም ድንቅ ነገር፣
አንደበት አይገልፀው ሁሉን ለመዘርዘር።
ለውለታህ ብዛት አፀፋ ከፈልኩህ፣
ደግ ውለህ ጌታዬ ልጅህ አሳዘንኩህ።
ብትጠራኝ ተሸሸግሁ ድምፅህን ሰምቼ፣
ዕራቁቴን ብሆን የኔ አምላክ ፈርቼ
ቅጠል ሰፋሁና ግልድም አገለደምኩ፣
ዕራቁትነቴን ልጅህ ተገነዘብኩ።

### ሔዋን

የሠራሁት ሥራ ጌታዬ አሳፈረኝ፣
ሰውን ያህል ነገር የእባብ ቃል አሞኘኝ።
ሁሉ በእጄ ሆኖ በረከት ሳይጎለኝ፣
ዕውቀትና ጥበብ ላይጠቅም ደለለኝ።
አትንኩ ካልከው ዛፍ አስቀድሜ ነካሁ፣
ቃልህን አፍርሼ የእባቡን ቃል ሰማሁ።
የጓጓሁት ጥበብ ዕውቀቴ ሲለካ፣
ድምፅህን ሰምቼ መደበቅ ነው ለካ።
አባት ሰውነቴን ክብር እንዳልሸፈነኝ፣
ጸጋዬ ቢጓደል ቁርበት አለበስከኝ።

### አዳም

መጠበቂያዬ ላይ ሳታገኝኝ ቀርተህ፣
ያለ መታመኔ ሥራዬ አሳዘነህ።
ከአንተ መደበቄ መሸሼ ሳይረዳኝ፣
«አዳም ወዴት አለህ» የሚል ቃል ተሰማኝ።
ብቻዬን እሆን ዘንድ መልካም ስላይደለ፣
ረዳት ሰጠኸኝ እኔን የመሰለ።

በቃል አሸንፏት እባብ መክሯት ሰምታ፣
የሰጠኸኝ አጋር አሳተችኝ ስታ።
አብረን በላንና አብረን ተደበቅን፣
ዕራቁት መሆንን መፍራትን ዐወቅን።

### ሔዋን

ለበለጠ ክብር የበላሁት ፍሬ፣
ለውርደት ሆነብኝ ተደበቅሁ አፍሬ።
ዕለቱን አጥፍቼ ዕለቱን ታወቀኝ፣
የበላሁት ፍሬ ከፊትህ አሸሸኝ።
እንደ ወትሮህ መጥተህ ባስቀመጥከን ስፍራ፣
ሳታገኘን ቀርተህ ሰማን ስትጣራ።
እባብ አሳይቶኝ ከቀጠፍኩት ፍሬ፣
አብረን እንድንከብር ሰጠሁት ለአጋሬ።
ያለ አንተ መኖሩን ሳንገፋው ጀምረን፣
ዛፉ ሥር ተደበቅን ቅጠል አገልድመን።

### አዳም

እኔና ሴቲቱ ሲከፈት ዓይናችን፣
በግልጽ ታወቀን ባዶ መሆናችን።
አትብሉት ያልከውን ፍሬ በመብላቴ፣
በግልጽ ታወቀኝ አባት ባዶነቴ።
መደበቄን አውቀህ «ወዴት አለህ አልከኝ»፣
አባት በጨለማው ቀን ሲመሽ ጠራኸኝ።
በይፋ ስትነግረኝ ፍጹም ባዶነቴን፣
«ማን ነገረህ» አልከኝ ዕራቁትነቴን።

መልስ አጣሁ ለቃልህ ጥያቄው ከበደኝ፣
ዕራቁትነቴን ማንም አልነገረኝ።
እኔ ነኝ ያወቅሁት ከበላሁ በኋላ፣
በሐዘን ሲለወጥ የነበረኝ ተድላ።
እንደዚህ ልፈራህ ስታነጋግረኝ፣
ካልታዘዘው በላሁ ሴቲቱ ብትሰጠኝ።

# ሔዋን

በምሳሌህ ፈጥረህ ሕያው ያደረግኸኝ፣
እግዚአብሔር አምላኬ ጥያቄህ ደረሰኝ።
ቅጠል አገልድሜ ካለሁበት ቦታ፣
ከአዳም ተነጋግረህ ቀኑ ሲመሽ ጌታ፣
«በላህ ወይ» ስትለው ካልታዘዘው ፍሬ፣
እንቀጠቀጥ ነበር በሥራዬ አፍሬ።

«ይኼ ያደረግሽው ምንድን ነው» ስትለኝ፣
እግዚአብሔር ነገርኩህ እባቡ እንዳሳተኝ።
መቅጠፍ ሳይገባኝ ከፍሬው ወሰድኩኝ፣
እኔም በላሁና ለአዳምም ሰጠሁኝ።

ዓይኔ ተከፈተ ዕራቁቴን ቀረሁ፣
ሞት ማለት ይሄ ነው ከፊትህ ተለየሁ።
እንዲያ እንዳልተደሰትኩ በኤደን ከተማ፣
ፈራሁ ተንቀጠቀጥኩ ድምፅህን ስሰማ።

# አዳም

ጌታ አትፍረድብኝ አንተ ባትሰጠኝ፣
ሔዋንን ከጎኔ አጋር እንድትሆነኝ፣
ማን ያበላኝ ነበር ከፍሬው በጥሶ፣
መች ይቀየር ነበር ደስታዬ በለቅሶ።

ሔዋን ሳንማከር ለብቻሽ ተስማምተሽ፣
ላይሆን ጓደኝነት ከእባቡ ጋር ገጥመሽ፣
ይሻለኝ ነበረ መኖር ለብቻዬ፣
ከአምላክ ካጣላሽኝ ሔዋን ጓደኛዬ።

# ሔዋን

አዳም አንተ አይደለህ ጥንቱን የፈጠርከኝ፣
እግዚአብሔር አይደል ወይ ትንፋሽ የለገሠኝ።
ከእግዚአብሔር አትበልጥም አዳም አትሳሳት፣
ለጥፋት አይደለም የኔ ምድር መምጣት።

የመጀመሪያው ቀን ስታየኝ ሳገኝህ፣
ብለህ አልነበር ወይ አጥንቴ ከአጥንትህ።
ያላሰብኩት ነገር የጸብ ቀን ሲመጣ፣
ምነው ፊት ነሳኸኝ መንፈስህ ተቆጣ?

# አዳም

የፈጠረን አምላክ ሔዋን ሲያገናኘን፣
«ብዙና ተባዙ ምድርን ሙሏት» ያለን፣
መብል ይሆነን ዘንድ ሕይወት የለገሠን፣
የሚያፈራውን ዛፍ ሐመልማል የሰጠን፣
ከዚያ ለምለም ስፍራ ከገነት አስወጣን፣
ታማኝ ስላልሆንን ከአደራ ዛፍ በላን።
የአንቺን ቃል ሰምቼ ትእዛዝ ስላፈረስኩ፣
በኔ የተነሣ ምድሪቱን አስረገምኩ።
በሕይወት ዘመኔ ሳልደክም እንዳልበላ፣
ምድር ታበቅላለች እሾህ አሜከላ።
በመዳፉ ቀርፆ ሕይወት የለገሠኝ፣
«አፈር ነህ ወደ አፈር ትሄዳለህ» አለኝ።
ባትሰጪኝ ኖሮ ያንን የዛፍ ፍሬ፣
አንገቴን ባልደፋሁ እንደዚህ አፍሬ።

# ሔዋን

ሁሉን ቀድሜ ባውቅ ምን እንደሚገጥመኝ፣
«ተወኝ» እለው ነበር ያ እባብ ሲያናግረኝ።
«አትሞቱም» ስላለኝ በልቼ አበላሁህ፣
ካገኘሁት ፍሬ የታል የሰሰትኩህ።
ለኔስ መች ቀረልኝ በአንተ የደረሰው፣
ያለ ጭንቅ አልወልድም ፈቃዴም ለአንተ ነው

«ብዙና ተባዙ» ያለው ቃል ሲፈጸም፣
በፀነስኩኝ ጊዜ አያጣኝም ሕመም።
ብዙ እንድምሠቃይ እጅግ መጨነቄን፣
እግዚአብሔር ሲነግረኝ ታውቅ የለም ወይ የኔን

ምክንያት ብሆንም ስለመሳሳትህ፣
ለኔም ለአንተም ያው ነው ጥፋቴ ጥፋትህ።
በኔ ብታመካኝ በእባቡ አመካኘሁ፣
አንተም ሳትድን ቀረህ እኔም ሳልድን ቀረሁ።

# አዳም

ቢያምነን አልነበር ወይ የዚህ ዓለም ጌታ፣
ከገነት አግብቶ ያስረከበን ቦታ።
ቃል አጠፍን ሔዋን እምነታችን የታል፣
ምድር ፍሬ ሞልቷት አደራ በልተናል።

የወደድሸው ጥበብ ለመልካም ያሰብሸው፣
ከእግዚአብሔር ለያየን ቀጥፈሽ ያመጣሽው።
ሔዋን ሳናስበው ሳንዘጋጅበት፣
አደራ የሰጠን ከተፍ አለ ድንገት።

## ሔዋን

እስኪአትፍረድ አዳም ፍርዱን ለአምላክተወው
ከንቱ አትናገረኝ የልቤን ሳታውቀው።
የኔ ብቻ ቢሆን የጥፋቱ ነገር፣
አንተ ገነት ቀርተህ እኔ እባረር ነበር።
ብሰጥህ ተቀበልክ ብበላ በልተኻል፣
ከገነት መካከል መቅጠፌን አውቀኻል።
አዳም አብረን በልተን ቆርሰን ከገበታ፣
ምነው አሳልፈህ ሰጠኸኝ ለጌታ።

## አዳም

አጥንቴና አጥንትሽ አንድ ናቸው ብዬ፣
ሥጋዬና ሥጋሽ ተስማምተዋል ብዬ፣
መንፈሴ መንፈስሽ ተገናኝቷል ብዬ፣
የሚስቴን ቃል ሰማሁ የአባቴን ቃል ጥዬ።

## ሔዋን

መብላት ስላልፈቀድኩ ካንተ ተሠውሬ፣
ያለኝን ላካፍል ይዤ መጣሁ ፍሬ።
የእጄን ሳቀርብልህ መች አልከኝ አልበላም፣
እኔም ተሳሳትኩኝ አንተም ቸኮልክ አዳም።

## አዳም

ሁሉን አስረክቦን የምድርን በረከት፣
በደስታ በተድላ ስንኖር በገነት፣
በጸጋ ተሞልተን እያለን በሕይወት፣
ክብራችን ተለየን ባመጣሽው ስሕተት።

## ሔዋን

ሆን ብዬ አላጠፋሁ በኔ አትፍረድ አዳም፣
መግደሉን ባውቅማ እጄን አልዘረጋም።
አልሆን አለኝ እንጂ አጋሬን መዘንጋት፣
መች ይጠፋኝ ነበረ አንተ ሳታይ መብላት።

## አዳም

አትብሉ መባሉን አትቅጠፉ ቅጠል፣
ሔዋን ሰምተሽ ነበር ከገነት መካከል።
ጽናትሽ የት ሄደ ምነው ቶሎ ረሳሽ፣
ያምላክን ቃል ትተሽ እንዴት የእባብ ሰማሽ።
ሲያልፍ ነው ጸጸቱ የእጄን ክብር አጣሁ፣
አንቺም የእባቡን ቃል እኔም የአንቺን ሰማሁ።
ብዙ ነገር ነበር የተፈቀደልን፣
ከገበታው ውጪ በልተን ተታለልን።
የቀጠፍሽው ቅጠል መች ለዕውቀት ጠቀመሽ፣
ያናገረሽ እባብ በምን ቃል ደለለሽ??
ምን አለሽ እባቡ ሔዋን ተናገሪ፣
አረ «ምን ሹክ አለሽ» ጌታን እንዳትፈሪ?
የማስጠንቀቂያው ቃል አልታወስ ያለሽ፣
«እንዳትበሉ» ብሎ እግዚአብሔር ያዘዘሽ።
እንግዳ ሆነብኝ ድርጊትሽ እያደር፣
ሔዋን የሠራሽው ያደረግሽው ነገር።

## ሔዋን

ሰሚ አጣሁኝ እንጂ ልቤም ተሰበረ፣
ላሳሳተኝ እባብ ነግሬው ነበረ።
ከገነት መካከል ካለው ፍሬ መብላት፣
ሞት ያመጣል ብዬ ያስከትላል ቅጣት፣
ለዓይን የሚያስጎመጅ በለስ አመላክቶኝ፣
ምግብ ከአባቴ ጋር አስቀረ አለያይቶኝ።

ከትእዛዝ መውጣቴ ቃል - መሻሬ ገባኝ፣
እባብ ከፈጣሪ ከጌታዬ አጣላኝ።
ሰላምታ ደርድሮ ንግግር ጀመረኝ፣
አትሞቺም ብሎ በቃል ሸነገለኝ።
የዛፉን ላይ ፍሬ እንድቀጥፍ አሳየኝ፣
ብበላ እንደማልሞት አድርጎ ነገረኝ።
እንዳልተፈቀደ ተናገርኩ አስረዳሁ፣
ብቻዬን ሆንኩና በሙግት ተረታሁ።

## አዳም

ሞልቶ ተርፎ ነበር በምድር የተሰጠን፣
ዓይንሽ አይቶ ጓጉቶ ለሞት አደረሰን።
ቀን ጣለን ይባላል ወይስ ተሳሳትን?
ሔዋን ከእግዚአብሔር ፊት አፍረን ተደበቅን።

የተሰጠንን መብት እንደ ዋዛ አጣነው፣
ግብራችንን አውቀን ሸሽን ላናመልጠው።
«ወዴት ነህ» የሚል ቃል ከአምላካችን መጣ፣
ቃል በማፍረሳችን ሰማነው ሲቆጣ።
የሚያሳዝን ድርጊት በመፈጸማችን፣
የነበረን ተድላ ጠፋ ከውስጣችን።

## ሔዋን

ሳንድን ቀረን እንጂ ሳይጠቅመን ሰበቡ፣
አንተ በኔ ብትፈርድ ፈረድኩኝ በእባቡ።
አመካኝቶ መዳን እንደሌለ አወቅኹኝ፤
ቅጣትን ከእግዚአብሔር እንደ አንተ አገኘሁኝ
በሠራሁት ሥራ ሁልጊዜ አለቅሳለሁ፣
አደራ መወጣት ሳልችል ቀርቼአለሁ።
እንዲመልስልን የፊቱን ደስታ፣
እስኪ ጌታችንን «እንለምን ይቅርታ።»

## አዳም

ዋሸቶ ያታለለሽ የጥፋት ጓደኛሽ፣
ወዴት ሄደ ዛሬ መች መጣ ሊያጽናናሽ።
ቀርቦ ያታለለሽ ያዘናጋሽ ሔዋን፣
ሳይችልበት ቀረ እራሱን ለማዳን።
አጉል ምክር መክሮ ከአምላክ ያለያየሽ፣
አይዞሽ! ሲል አልመጣም ከዛፍ ሥር እያለሽ።

## ሔዋን

የምትድን መስሎኝ አመካኝተህ በኔ፣
በእባቡ አመካኘሁ እድን መስሎኝ እኔ።
ስንደበቅ እንጂ አብረን የነበርነው፣
አዳም ስንበላ እንጂ ሕብረት ያደረግነው፣
ስንጠየቅማ ጌታ ሲያናግረን፣
«እርስዋ ናት እርሱ ነው» ተባብለን ቀረን።

## አዳም እና ሔዋን

ከቀላል ቆጥረነው የእጃችንን ዋጋ፣
ሲነጠቅ ታወቀን የነበረን ጸጋ።
ጠፍተን እንደማንቀር ተስፋ የለገሰን፣
አይቀርም ይመጣል ዳግም ሊጎበኘን።

ከነበረን ክብር ከነበረን ቦታ፣
«መልሰን» እንበለው ይመልሳል ጌታ።

የእጃችንን ዕንቁ ሀብታችንን አጣን፣
«ከቤትህ ወጥተናል ከአሳብህ አታውጣን።»
ከአንተ ቤት ያለውን የትናንቱን ኑሮ፣
ተድላ ደስታውን ለወጥነው በእሮሮ።

«ቸር ነህ ቸር ዋልልን» ባለንበት ቦታ፣
በምሕረትህ ጎብኘን አርግልን ይቅርታ።
አባታችን ዳግም ልጅነትን ስጠን፣
በእንባና በጸሎት እንለምንሃለን።

ሞት ቀምሰናልና እኛ ቃል አፍርሰን፣
በቃልህ ተገኝተህ በምሕረትህ ዳብሰን።
የተድላህን ፈሳሽ የሕይወትን ምግብ፣
አባት ሆይ ለግሰን በልተን እንድንጠግብ!!

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር!**

**አብርሃም ሰሎሞን**
ABRAHAM SOLOMON

**የካቲት ፫/፲፱፻፺፩**